# የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲ ግንባር

# (ኢህአዴግ)

# መተዳደሪያ ደንብ

*መስከረም 1999 ዓ.ም*

# የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር /ኢህአዴግ/ መተዳደሪያ ደንብ

## I. መግቢያ፣

ኢህአዴግ በአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ፕሮግራም የሚመራና በፕሮግራሙ ላይ ለሰፈሩት አላማዎች የሚታገል ድርጅት ነው:: ያነገባቸው አላማዎች ዴሞክራሲያዊና አብዮታዊ በመሆናቸው በተግባር ላይ ከዋሉ ህብረተሰባችንን ከሚገኝበት ድህነትና ኃላቀርነት አላቅቀው ለፍትህ፣ ለዴሞክራሲና ለብልፅግና ያበቁታል:: በመሆኑም ኢህአዴግ የኢትዮጵያን ህብረተሰብ ለመለወጥ ቁልፍ መሳሪያ የሆነውን አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ፕሮግራሙን በተግባር ላይ ለማዋል በሙሉ አቅሙ ይረባረባል::

ኢህአዴግ ያነገባቸው አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አላማዎች በአስተማማኝ ሁኔታ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉት ምልአተ-ህዝቡ ተገንዝቧቸውና ከልብ አምኖባቸው ለተግባራዊነታቸው ሲረባረብ ነው:: ሰፊው የአገራችን ህዝብ በአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አላማዎች ዙሪያ ተሰባስቦ ለፕሮግራሙ ተግባራዊነት እንዲረባረብ ለማድረግ ደግሞ ኢህአዴግ ሙሉ ድርጅታዊ አቅሙን አስተባብሮ ህብረተሰቡን የማንቃት፣ የማደራጀትና በተቀናጀ አግባብ ለተግባራዊ እንቅስቃሴ የማሰለፍ ግንባር ቀደም ሚና መጫወት ይጠበቅበታል::

ኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ፕሮግራሙን በስራ ላይ ለማዋል በሚያስችል ደረጃ ምልዐተ-ህዝቡን የማንቀሳቀስ ግንባር ቀደም ሚና ሊጫወት የሚችለው በኢህአዴግና በአባል ድርጅቶቹ ውስጥ ከላይ እስከታች አስተማማኝ የሀሳብና የተግባር አንድነት ሲኖር ነው:: በግንባሩም ሆነ በአባል ድርጅቶቹ ውስጥ ይህን የሀሳብና የተግባር አንድነት ለመፍጠርና በቀጣይነት ለማጎልበት እንዲቻል በድርጅት ውስጥ ብልጭ ድርግም የማይል አስተማማኝና ቀጣይነት ያለው ዴሞክራሲያዊ መድረክ ያስፈልጋል:: በሀሳቦች መካከል ነፃና ዴሞክራሲያዊ ትግል የሚካሄድበት ዘላቂ ህጋዊና ተቋማዊ ሁኔታ ሊኖር ይገባል:: መተዳደሪያ ደንባችን በኢህአዴግና በአባል ድርጅቶቹ ውስጥ የሀሳቦች ትግል በነፃነት መንፈስ የሚካሄድበትን ዴሞክራሲያዊ መድረክ ህጋዊና ተቋማዊ መልክ በማስያዝ አስተማማኝ እንዲሆን ያደርገዋል:: በመሆኑም መተዳደሪያ ደንባችን፣

በድርጅታችን ውስጥ አስተማማኝ ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ በመፍጠር ለዳበረ የሀሳብ አንድነት የሚያበቃን በመሆኑ መላ አካላትና አባላት በዝርዝር ሊገነዘቡትና ለተግባራዊነቱ ሊታገሉለት ይገባል፡፡

መተዳደሪያ ደንባችን ህጋዊና ተቋማዊ መልክ ባገኘው ዴሞክራሲያችን በመጠቀም የምንፈጥረው የሀሳብ አንድነት በተጠናከረ የተግባር አንድነት እንዲገለፅ ለማድረግም ያስችለናል፡፡ ዴሞክራሲ ህጋዊና ተቋማዊ መልክ መያዙ በሀሳቦች መካከል ለሚካሄድ ነፃ ትግል አስተማማኝ ሁኔታ ይፈጥራል እንጂ ልዩነትን ጨርሶ ያስወግዳል ማለት አይደለም፡፡ የዴሞክራሲ መስፈን በግንባሩና በአባል ድርጅቶቹ ውስጥ በፕሮግራም ጉዳዮችም ሆነ ከፕሮግራም በመለስ ባሉ ጉዳዩች ላይ ልዩነት እንዳይነሳ አያደርግም፡፡ ዴሞክራሲው ልዩነት እንዳይነሳ ወይ እንዲጠፋ ሳይሆን ልዩነቶች የግንባሩን የትግል አንድነት ሳያናጉ ስርአት ባለው መንገድ እንዲገለፁ ለማድረግ የሚያስችል ነው፡፡

መተዳደሪያ ደንባችን ከዴሞክራሲው ጎን ለጎን የብዙሀኑ ፍላጎት የተግባር መመሪያ እንዲሆንና በተግባር እንዲተረጎም ለማድረግ የሚያስችል ገፅታም አለው፡፡ ያለዚህ የተግባር አንድነት ድርጅታችን ከውይይት ክበብ የተለየ ሊሆን አይችልም፡፡ በመሆኑም መተዳደሪያ ደንባችን በአንድ በኩል ለነፃና ግልፅ የሀሳብ ትግል አመች የሆነውን ዴሞክራሲያዊ መድረክ በማስፈን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ለብዙሀኑ ፍላጎት ተግባራዊ መሆን የሚያበቁ የጋራ ግዴታዎችን በውል ለይቶ በመደንገግ ግንባራችንና አባል ድርጅቶቹ ለጠንካራ የሀሳብና የተግባር አንድነት እንድንበቃ ያስችለናል፡፡ በመሆኑም መተዳደሪያ ደንባችን በስራ ላይ እንዲውል አጥብቀን ልንታገልለትና እንደአይናችን ብሌን ልንጠብቀው ይገባናል፡፡

ኢህአዴግ የበርካታ ብሄራዊ ድርጅቶች የህብረት ግንባር ነው፡፡ አባል ድርጅቶቹ የኢህአዴግን ፕሮግራም ከአካባቢያቸው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አጣጥመው ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡ አገራዊ ጉዳዮችን ደግሞ በዚሁ ፕሮግራም አማካይነት በጋራ ይመራሉ፡፡ የኢህአዴግ መተዳደሪያ ደንብ በክልልና በአገር ደረጃ የምንሰጠው የፖለቲካ አመራር በጠራ የስራ ክፍፍል የሚመራ እንዲሆን ግንባሩና አባል ድርጅቶቹ የሚኖራቸውን የሀላፊነትና የተጠያቂነት ወሰን በግልፅ ይደነግጋል፡፡ ኢህአዴግም ሆነ እያንዳንዱ አባል ድርጅት የሚኖረውን መብትና የሚጠበቅበትን ግዴታ በመወሰን መብቶች ሲጣሱም ሆነ ግዴታዎች በተሟላ አኳኋን ሳይፈፀሙ ሲቀሩ መፍትሄ የሚያገኙበትን ስርአት አካቶ

ይዟል፡፡ በመሆኑም መተዳደሪያ ደንባችን በኢህአዴግና በአባል ድርጅቶቹ መካከል ተመጋጋቢና ተደጋጋፊ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የሶሻል እንቅስቃሴ ለማድረግ በማስቻል የአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ፕሮግራማችንን አስተማማኝ ተፈፃሚነት ያረጋግጣል፡፡

የኢህአዴግ መተዳደሪያ ደንብ በኢህአዴግ ውስጥ የሚቋቋሙ ልዩ ልዩ አካላትና በነዚህ አካላት ውስጥ ተመድበው የሚሰሩ የግንባሩ አባላት ተግባርና ሀላፊነት ምን እንደሆነ፣ የውሳኔ አሰጣጥና አፈፃፀም ሂደት፣ እንዲሁም መዋቅሮቹ የሚጠቀሙባቸው የአሰራርና የአመራር መርሆዎች ምን እንደሆኑ በዝርዝር በማስቀመጥ ህጋዊና ተቋማዊ ስርአት ያለው ግንባር እንድንሆን ያበቃናል፡፡

የኢህአዴግ መተዳደሪያ ደንብ በከፍተኛ የአመራር አካላት ደረጃ የመተዳደሪያ ደንብ በሚጣስበትም ሆነ የአተረጓጎም ችግሮች በሚያጋጥሙበት ጊዜ ችግሮቹ እንዴት መፈታት እንዳለባቸው ግልፅ አቅጣጫዎችን ያስቀምጥልናል፡፡ በማጠቃለል መተዳደሪያ ደንባችን በግንባሩና በአባል ድርጅቶቹ እንዲሁም በግንባሩ የአመራር አካላትና አባላት መካከል ጠንካራ የሀሳብና የተግባር አንድነት፣ በግለሰባዊ ትስስር ምትክ በተቋማዊ አሰራር ላይ የተመሰረተ የአሰራርና የአመራር ስርአት እንዲኖረን በማድረግ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አላማዎቻችን በአስተማማኝ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ ያስችለናል፡፡

## II. ኢህአዴግ የሚመራባቸው አጠቃላይ የአደረጃጀት መርሆዎች፣

1. በአገራችን ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ሊገነባና ፈጣን ልማት እውን ሊሆን የሚችለው አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አላማ በተግባር ላይ ሲውል በመሆኑ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ድርጅቶቻችን ለአላማዎቻችን ተፈፃሚነት በፅናት የመንቀሳቀስና የጥገኝነትና የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከቶችንና ተግባራዊ እንቅስቃሴዎችንም በፅናት የመመከት ግዴታ አለባቸው፡፡ ለግንባሩ አላማዎችና ለመተዳደሪያ ደንቡ ተግባራዊነት በታማኝነትና በፅናት መታገልም ሀላፊነታቸው ነው፡፡

2. ኢትዮጵያ ህብረ-ብሄራዊ አገር እንደመሆኗ የተለያዩ ብሄሮቿንና ህዝቦቿን በአንድነት አሰባስቦ ለማታገል የሚቻለው ግለሰቦችን በተናጠል በሚያሰባስብ ህብረ-ብሄር ድርጅት ሳይሆን የድርጅቶች በተለይ ደግሞ የብሄር/ብሄረሰብ ድርጅቶች ግንባር በሆነ አደረጃጀት አማካይነት ነው፡፡ ምክንያቱም የድርጅቶች

በተለይም የብሄር/ብሄረሰብ ድርጅቶች በአንድነት ብቻ ያዋቀሩት ግንባር የሚከተሉትን ሁለት መሰረታዊ ጥያቄዎች የማሟላት ችሎታ ያለው በመሆኑ ነው፡፡

ሀ/ የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች የብሄር ብሄረሰብ ድርጅት በመመስረት መብታቸውንና ጥቅማቸውን በተሻለ ሁኔታ ለማስጠበቅ እንደሚፈልጉና እንደሚችሉ በተግባር እየታየ ነው፡፡ ብሄር ብሄረሰቦች የተሻለ ድርጅታዊ አመራር ለማግኘትና በፖለቲካ ሂደቱ በበለጠ መሳተፍ የሚችሉት በብሄር/ብሄረሰብ ድርጅቶቻቸው አማካይነት ሲታገሉ እንደሆነም አሁን ያለው ተጨባጭ እውነታ ያረጋግጣል፡፡ በመሆኑም እያንዳንዱ ብሄር መብቱንና ጥቅሙን በብሄራዊ ድርጅቶቹ አማካይነት ለማስጠበቅ ያለውን ፍላጎት በተሻለ ደረጃ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ ኢህአዴግ እንደ ህብረ-ብሄር ድርጅት የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦችን ጥቅም ማስጠበቅ አላማው ያደረገ በመሆኑ የብሄር ብሄረሰቦችን መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ የተደራጁ ብሄራዊ ድርጅቶችን ማቀፍ ይኖርበታል፡፡

ለ/ ብሄራዊ ድርጅቶች የሚመሩበትን አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ፕሮግራም በየክልላቸው ተግባራዊ በማድረግ የብሄር/ብሄረሰባቸውን ሰፊ ህዝብ መብትና ጥቅም ለማስከበር ያለሙ አደረጃጀቶች ናቸው፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በአገራችን ውስጥ በሚገኙ ልዩ ልዩ ብሄር ብሄረሰቦች ሰፊ ህዝብ መካከል ፅኑ ወንድማማችነትና አንድነት ለማዳበር ደግሞ በዴሞክራሲያዊ አላማዎች የሚመራ ህብረ-ብሄር አደረጃጀት ያስፈልጋል፡፡ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ የብሄር ብሄረሰብ ድርጅቶች በአንድ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር ዙሪያ መደራጀታቸው ይህን አላማ ተግባራዊ ለማድረግ የተሻለ አማራጭ ነው፡፡ ስለሆነም ኢህአዴግ የኢትዮጵያን ህዝቦች እኩልነትና አንድነት ለማስጠበቅ የሚታገል ድርጅት እንደመሆኑ አላማውን በተግባር ሊተረጉምና ሊያረጋግጥ የሚችለው የህዝቦቻቸውን መብት የማስጠበቅ አላማን ያነገቡና በቀላሉም የህዝባቸውን ድጋፍ የሚያገኙ የብሄር ብሄረሰብ ድርጅቶችን በግንባሩ ዙሪያ አሰልፎ ያንቀሳቅሳል፡፡

3. ኢህአዴግ ለአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አላማ ተግባራዊነት የሚንቀሳቀስ ድርጅት ስለሆነ በአባልነት ሊቀበልና ሊያሰባስብ የሚችለው አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አላማን በግልፅ በፕሮግራማቸው ላይ የቀረፁ ድርጅቶችን ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም ግንባሩ ማንኛውንም አይነት የብሄር ብሄረሰብ ድርጅት የሚያቅፍ ካለመሆኑም

በተጨማሪ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ፕሮግራሙን መቀበል ብቻም በኢህአዴግ ስር ለመሰባሰብ አያበቃም:: በተግባርም ለፕሮግራሙ ተፈፃሚነት መታገል ይጠይቃል:: በአባል ድርጅቶቹ የሚመለመሉ አባላትም ይህንኑ የሚያሟሉ መሆን ይኖርባቸዋል::

4. አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አላማ በአንድ ብሄር ብሄረሰብ ውስጥ ሊወከል የሚችለው በአንድ ድርጅት ብቻ ነው:: በመሆኑም በአጋጣሚ ምክንያት በአንድ ብሄር/ብሄረሰብ ውስጥ ቁጥራቸው ከአንድ በላይ የሆኑ ድርጅቶች በግንባሩ ስር ለመሰባሰብ ቢፈልጉ በቅድሚያ በአንድ ድርጅት መጠቃለል ወይም መዋሀድ ይኖርባቸዋል:: ምክንያቱም በአንድ ላይ ካልተጠቃለሉ ሁለቱ ወይም አንዱ ትክክለኛ አላማና አደረጃጀት ስለማይኖራቸው ነው:: በመሆኑም ግንባሩ ከአንድ ብሄር/ብሄረሰብ በአባልነት ሊቀበል የሚችለው አንድ ደርጅት ብቻ ነው::

5. የአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አላማ ተግባራዊ መሆን ጥቅማቸውን ሊያስከብርላቸው የሚችልና ከኢህአዴግ ጋር ተባብረው ለመስራት ዝግጁ የሆኑ የብሄር ብሄረስብ ድርጅቶችን በአጋርነት በጋራ የሚሰሩበት አደረጃጀት እንዲሁም ሌሎች ደጋፊዎችን የሚያሰባስብበት የደጋፊ አደረጃጀት ሊኖረው ይችላል::

6. የኢህአዴግን አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ኘሮግራም ተቀብለው ለተግባራዊነቱ ለመታገል የተዘጋጁና የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች አባላት የሆኑ ሴቶችና ወጣቶች በኢህአዴግ የሴቶችና ወጣቶች ሊግ ተደራጅተው እንዲንቀሳቀሱ ይደረጋል:: የሴቶች ሊግና የወጣቶች ሊግ የኢህአደግ አባላት ብቻ ሳይሆን የሊጉን አላማ የተቀበሉ ሌሎች ሴቶችና ወጣቶችም የሚደራጁበት፤ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብና ተግባር የሚጎለብት መድረክ በመሆን ይንቀሳቀሳል::

7. አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አላማ ተግባራዊ መሆን የሚችለው ለአላማው ቆሚለታለሁ የሚለው ድርጅት የተሟላ ዴሞክራሲያዊ ውስጣዊ ህይወትና አሰራር ሲኖረው ብቻ ነው:: በመሆኑም ኢህአዴግ አንድን ድርጅት በአባልነት የሚያሰልፈው በቅድሚያ አመልካቹ ድርጅት በአባላት ተሳትፎና ውሳኔ በዴሞክራሲያዊ መንገድ የተመረጡ የአመራር አባላት ያሉት መሆኑ፣ የአባላት ሀሳብን የመግለፅ ነፃነት መከበሩ፣ የዴሞክራሲያዊ ማእከላዊነት አሰራር መስፈኑ፣ የሂስ ግለሂስና የግምገማ አሰራር

መኖሩ፣ የድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ የበላይነትና ተፈፃሚነት ያለውና ግልፅ ህጋዊና ፍትሀዊ አሰራር የሰፈነበት መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው።

8. ኢህአዴግ የድርጅቶች አንድነት መገለጫ የሆነ ግንባር እንደመሆኑ መጠን ድርጅቶች ግንባሩን የሚቀላቀሉት አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ፕሮግራሙንና መተዳደሪያ ደንቡን ተቀብለው ነው። በመሆኑም ከግንባሩ የተለየ ፖለቲካዊና ርዕዮተ-አለማዊ ህልውና አይኖራቸውም። ከዚህ በመነሳት የኢህአዴግን አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አላማዎች በየክልላቸው የማስፈፀምና ኢህአዴግ በአገር አቀፍ ደረጃ የሚወስናቸውን ውሳኔዎች ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ አለባቸው። ሆኖም እያንዳንዱ የግንባሩ አባል ድርጅት የግንባሩን ፕሮግራምና አጠቃላይ እቅዶች ከራሱ ክልላዊ ሁኔታ ጋር የማጣጣም፣ ውስጠ-ድርጅት ህይወቱን የማከናወን፣ ወደግንባሩ ልዩ ልዩ አካላት የሚልካቸውን ተወካዮች ራሱ መርጦ የመላክና ሲፈልግም የመቀየር ነፃነት ይኖረዋል። ግንባሩን በፍላጎት እንደተቀላቀለው ሁሉ በአባልነት መቀጠል ባልፈለገበት ጊዜም ለቆ የመውጣት ነፃነቱ የተጠበቀ ነው። ሆኖም ግንባሩን ለቆ የመውጣት ጉዳይ የሚፈፀመው በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ በዝርዝር በሰፈሩት አንቀፆች መሰረት ይሆናል።

9. ኢህአዴግ አንድነቱን በመጠበቅ ተጠናክሮ ፖለቲካዊ ፕሮግራሙን ማሳካት የሚችለው በአባል ድርጅቶቹ መካከል እኩልነት ሲኖር ነው። የበርካታ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ድርጅቶች ግንባር እንደመሆኑ መጠን በድርጅቶቹ መካከል የሚኖር ግንኙነት ከእኩልነት ውጭ ሊታሰብ የሚችል አይሆንም። በመሆኑም አባል ድርጅቶቹ በሙሉ ተመሳሳይ መብትና ግዴታ ኖሯቸው በጋራ ጉዳዮች ላይ በእኩልነት የመምከር፣ በውሳኔ አሰጣጥ የመሳተፍና በግንባሩ የአመራር አካላት ውስጥ በእኩልነት የመወከል መብት አላቸው።

# ምዕራፍ አንድ

# ጠቅላላ

## አንቀጽ 1 ርእስ

ይህ መተዳደሪያ ደንብ «በኢህአዴግ ስድስተኛ ድርጅታዊ ጉባኤ ተሻሽሎ የፀደቀ የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር /ኢህአዴግ/ መተዳደሪያ ደንብ» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 2 የግንባሩ መጠሪያ

የግንባሩ መጠሪያ "የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር" /ኢህአዴግ/ ነው፡፡

## አንቀጽ 3 የግንባሩ አርማ

መደቡ ቀይ ሆኖ በስተቀኝ የስንዴ ዛላ በስተግራ መዘውርና በግማሽ ክብ ቅርጽ የተጣመሩበት፤ በሁለት እጆች የተያዘ ችቦ መሀል ለመሀል የሚገኝበት፤ ከችቦው አናት በመዘውሩና በስንዴው ዛላ ጫፎች መካከል ቢጫ ኮከብ ያለው ነው፡፡

## አንቀጽ 4 የአርማው ትርጉም

1. ቀዩ መደብ ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ የተከፈለውን ክቡር መስዋዕት ያመለክታል፡፡
2. የስንዴው ዛላ፣ መዘውሩና ችቦው በገጠርና በከተማ የሚገኙ በኢህአዴግ ዙሪያ የተሰባሰቡ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ማህበራዊ መሰረት የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ይወክላል፡፡
3. ሁለቱ እጆች ህዝቦች በአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ዙሪያ መነሳታቸውንና የትግል አንድነታቸውን ያመለክታል፡፡

4. ኮከቡ በአገራችን ዘላቂ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመገንባት ያለንን ብሩህ ተስፋ ይወክላል::

## አንቀጽ 5 የግንባሩ ልሳን

1. የግንባሩ ልሳን «አብዮታዊ ዴሞክራሲ» ነው::
2. ልሳኑ የግንባሩ የስራ ቋንቋ በሆነው በአማርኛ ይዘጋጃል::
3. ከላይ በንኡስ አንቀጽ 2 የተጠቀሰው ቢኖርም በተለያዩ ቋንቋዎች የሚዘጋጁ የአባል ድርጅቶች ልሳኖችም የኢህአዴግ ይፋ አቋሞች የሚገለጽባቸው ጋዜጦች ሆነው ያገለግላሉ::

# አንቀጽ 6 የግንባሩ ዋና ጽህፈት ቤት

የግንባሩ ዋና ጽህፈት ቤት አዲስ አበባ ይሆናል::

# አቀጽ 7 የግንባሩ የአደረጃጀትና የአሰራር መርሆዎች

1. የግንባሩ የአደረጃጀት መርሆዎች
   ሀ. ኢህአዴግ በአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ድርጅቶች ህብረት የተፈጠረ ግንባር እንጂ ግለሰቦችን በተናጥል በመመልመል የተዋቀረ ግንባር አይደለም::
   ለ. ሁሉም የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች አገራዊውን አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ፕሮግራም በየክልላቸው የመፈፀም ግዴታ አለባቸው::
   ሐ. ከላይ በ«ለ» የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ አባል ድርጅቶቹ የኢህአዴግን ፕሮግራም ከየክልላቸው ሁኔታ አጣጥመው የመፈጸም ድርጅታዊ ነፃነት አላቸው::
   መ. ኢህአዴግ እኩልነታቸው የተጠበቀ ድርጅቶች ግንባር ነው፣
   ሠ. በኢህአዴግ አባልነት የሚታቀፉ ድርጅቶች በዴሞክራሲያዊ መርሆዎች የሚመሩና የዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነትን አሰራር የሚከተሉ ብቻ ናቸው፣

ረ. ኢህአዴግ የአገሪቱን ህጎች መሰረት በማድረግና በማክበር ተግባራቱን ያከናውናል፣

2. የጋራ አሰራርና የግለሰብ ሀላፊነትን በተመለከተ

ሀ. በየደረጃው የሚገኙ የኢህአዴግ አካላት ማንኛውንም ውሳኔ የሚያሳልፉት በጉዳዩ ላይ በጋራ ከተወያዩ በኋላ በድምጽ ብልጫ ይሆናል፡፡

ለ. አንድ ሰው አንድ ድምጽ ብቻ ይኖረዋል፡፡ ለውሳኔ የቀረበ ሀሳብ የጋራ መመሪያ ሆኖ ሊያገለግል የሚችለው ከተገኘው ምልዐተ-ጉባኤ ከ50% +1 በላይ ድምጽ ካገኘ ነው፡፡ ተሰብሳቢው በእኩል ድምጽ ከተከፈለ ሊቀመንበሩ ያለበት ወገን ድምጽ አሸናፊ ይሆናል፡፡

ሐ. በመደበኛም ሆነ በአስቸኳይ ስብሰባዎች ላይ መገኘት ያለባቸው አባላት በሙሉ የመገኘት ግዴታ አለባቸው፡፡ ስብሰባ እንዳይጀመርም ሆነ ከተጀመረ በኋላ ሆን ብሎ ምልዐተ ጉባኤ እንዳይኖር ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

መ. በራሱ ፈቃድ ምልዐተ ጉባኤ  እንዳይሟላ ጥሎ የወጣ ሰው ራሱን እንዳሰናበተ ይቆጠራል፡፡ እያንዳንዱ ድርጅት በምትኩ ሌላ ሰው ይመድባል፤ ምደባው እስኪጠናቀቅ ድረስ ምልዐተ ጉባኤው የሚሰላው ከቀሩት አባላት ይሆናል፡፡ ይህም ሆኖ ግለሰቡ የተለየ ምክንያት አለኝ ካለ አቤቱታ የማቅረብ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

ሠ. ከ50%+1 ድምጽ በላይ ያገኘ የውሳኔ ሀሳብ በወሰነው አካልና ከሱ በታች ባሉ አካላትና አባላት በሙሉ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

ረ. በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ተለይተው ከተደነገጉት በስተቀር በየትኛውም አካል ስብሰባ ላይ ምልዐተ-ጉባኤ ተሟልቷል የሚባለው ከጠቅላላ የስብሰባው ተካፋዮች 50%+1 ሲገኙ ነው፡፡

ሰ. በመደበኛም ሆነ በአስቸኳይ ስብሰባዎች ላይ መገኘት ያለባቸው አባላት በሙሉ የመገኘት ግዴታ አለባቸው፡፡

ሸ. ማንኛውም የኮሚቴ ውሳኔ ተፈፃሚ የሚሆነው ለኮሚቴው አባላት በተናጠል ወይም ደግሞ ከኮሚቴው በታች ላሉ አካላትና አባላት በሚሰጥ የጋራ ወይም የተናጠል ሃላፊነት ይሆናል፡፡

ቀ. ማንኛውም የበታች ኮሚቴ ወይም የበታች ኮሚቴ አባል ከበላይ አካል የመጣለትን ውሳኔ የመፈጸም ግዴታ አለበት::

በ. በኮሚቴ ውሳኔዎች ቅር የተሰኘ ወይም ያልተስማማ አባል ውሳኔዎቹን እየፈፀመ ውሳኔው እንደገና እንዲታይ ህጋዊ በሆነ መንገድ የመጠየቅ መብት አለው::

ተ. በማንኛውም የውሳኔ ሀሳብ ላይ ከተሰብሳቢው አባል 1/3ኛ የሚሆኑት እንደገና እንዲታይ ጥያቄ ከቀረበ ጥያቄው ለውይይት ክፍት ይሆናል:: 50%+1 በላይ የሆኑት እንደገና መታየት አለበት ብለው ከወሰኑ ጉዳዩ እንደአዲስ ታይቶ ይወሰናል::

ቸ. በአንድ መድረክ በተወሰነ ውሳኔ ላይ አቤተታ ቀርቦ በዚያው መድረክ ተቀባይነት ካላገኘ ድጋሚ አቤቱታ አይቀርብም:: በጉደዩ ላይ አቤቱታ ማቅረብ የሚቻለው ውሳኔውን በተግባር እየፈፀሙ በሂደት በሚከፈት የስብሰባ አጋጣሚ ወይም የፅሁፍ ፊርማ በማሰባሰብ ብቻ ይሆናል::

ኀ. እንደገና ይታይልን የሚል ጥያቄ የወሰነው አካል በስብሰባ ላይ ባለበት በቃል ወይም በፅሁፍ አቤቱታው ሲቀርብ ጉዳዩ ከላይ በ ’በ’ በቀረበው መሰረት ይታያል:: ወሳኙ አካል ከተበተነ ደግሞ በፅሁፍ አቤቱታ በመጠየቅ ሊቀርብ ይችላል:: በፅሁፍ የሚቀርብ አቤቱታ የሚቀርበው ህጋዊነትና ግልጽነት በተላበሰ አኳኋን ይሆናል:: አቤቱታ አቅራቢው ግለሰብ አቤቱታውን በፅሁፍ አዘጋጅቶ ለአካሉ ሰብሳቢ ያስረክባል:: ሰብሳቢው አቤቱታውን ወደሚመለከታቸው አባላት ሁሉ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ በማሰራጨት አቤቱታውን የሚደግፉ ሁሉ እንዲፈርሙ ያደርጋል:: ከሚመለከታቸው አባላት ውስጥ 1/3ኛው ከፈረሙ ጉዳዩ በሚቀጠለው መደበኛ ስብሰባ ወይም ደግሞ እንደአመችነቱ ቀደም ብሎ በሚጠራ አስቸኳይ ስብሰባ ላይ እንዲታይ ይደረጋል::

3. የኢህአዴግ አሰራሮች በግልፅነትና በተጠያቂነት ላይ የተመሰረቱ ይሆናሉ::

ሀ. የበላይ አካላት ውሳኔዎች በተለየ ሁኔታ በምስጢር ተጠብቀው እንዲቆዩ ካልተወሰነ በስተቀር በተዋረድ ለአባላት ይገለፃሉ::

ለ. በተለየ ሁኔታ በምስጢርነት ተጠብቀው ሊቆዩ የሚችሉ ጉዳዮች በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ጎራ ላይ ጉዳት የማስከተል ውጤት ያላቸው ጉዳዮች ብቻ ናቸው፡፡

ሐ. በኢህዴግ ከፍተኛ የአመራር አካላት የሚወሰዱና በአገሪቱና በህዝቦቿ ላይ ጉልህ ተፅእኖ የሚያሳርፉ አቋሞችን ሁሉ ከአስፈላጊው ማብራሪያ ጋር ለህዝብ በተገቢው ወቅት ይገለፃሉ፡፡

መ. ግንባሩ በመሰረታዊ ጉዳዮች ላይ የሴቶችንና ወጣት ሊጎችን እንዲሁም የተለያዩ ደጋፊ አደረጃጀቶችንና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን እያማከረ የሚሰራበት አግባብ እንዲዳብር ይደረጋል፡፡

መ. በየደረጃው የሚገኙ የኢህዴግ የአመራር አካላት የስራ እንቅስቃሴያቸውን የሚያሳይ ዝርዝር ሪፖርት በተመደበላቸው ወቅት ለበላይ አካላት ያቀርባሉ፡፡

ሠ. በየደረጃው የሚገኙ አካላት ለወሰኗቸው ውሳኔዎች ሁሉ ሀላፊነት ይወስዳሉ፡፡ በተጨማሪም ሀላፊነትን ባለመወጣት ወይም ከተሰጠ ሀላፊነት ውጭ ከተሰማሩ ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

ረ. ተጠያቂነቱ እንደሁኔታው በግንባሩ ወይም በሚመለከተው ድርጅት መተዳደሪያ ደንብ ወይም በአገሪቱ ህጎች መሰረት ሊፈፀም ይችላል፡፡

4. የኢህአዴግ ተግባራት በክልሎች ደረጃ ተፈፃሚ የሚሆኑት በአባል ብሄራዊ ድርጅቶች አማካኝነት ይሆናል፡፡

ሀ. ኢህአዴግ በአገር ደረጃ እንዲፈፀም ያወጣው ፕሮግራም የሚወስናቸው ውሳኔዎችም ሆነ የሚያወጣቸው እቅዶች አባል ድርጅቶች ባሉበት ክልል ተፈፃሚ የሚሆኑት በብሄራዊ ድርጅቶቹ አማካኝነት ይሆናል፡፡

ለ. ብሄራዊ ድርጅቶች አገራዊውን ውሳኔና መሰረታዊ የአፈፃፀም አቅጣጫ በክልላቸው ተፈፃሚ የማድረግ ግዴታ አለባቸው፡፡ ሆኖም አገራዊ ውሳኔዎችንና የአፈጻጸም አቅጣጫዎችን ከክልላቸው ተጨባጭ ሁኔታ አጣጥሞ የመፈፀም ድርጅታዊ ነፃነት አላቸው፡፡

ሐ. ኢህአዴግ በብሄራዊ ክልሎች ውስጥ ከብሄራዊ ድርጅቶቹ መዋቅር የተለየ ሌላ መዋቅር አይዘረጋም፡፡ ሆኖም በጊዜያዊነት ተልእኮ

የመፈፀም ሃላፊነት ወስደው በአካባቢው ከሚገኘው ብሄራዊ ድርጅት ጋር በቅንጅት የሚንቀሳቀሱ ጊዜያዊ ቡድኖችን ወይም ግለሰቦችን ለመላክ ይችላል፡፡

መ. ኢህአዴግ በአባል ድርጅቶች ውስጥ ከተናጠል ድርጅቱ አቅም በላይ የሆነ ችግር በሚያጋጥምት ጊዜ በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ወይም በምክር ቤቱ ውሳኔ መሰረት ችግር ያጋጠመውን ድርጅት በልዩ ልዩ አግባቦች ለማገዝ ይችላል፡፡ ሆኖም ይህ እገዛ የድርጅቱን ጥንካሬና ራስን ችሎ የመቆም ሂደት የሚያጠናክርና ለተወሰነ ጊዜ ብቻ የሚደረግ ሊሆን ይገባል፡፡

5. በፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች፣ ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች፣ በውጭ አገር በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እንዲሁም በኢህአዴግ በጋራ በሚመሩ ተቋማት የሚኖሩት የኢህአዴግ መዋቅሮች የድርጅት ተግባር በተመለከተ ተጠሪነታቸው ለኢህአዴግ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

ሀ. በነዚህ አካላት ውስጥ የሚሰራው ስራ ተጠሪነት ለኢህአደግ ጽ/ቤት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በተቻለ መጠን ከሁሉም ድርጅቶች ተውጣጥቶ በሚመሰረት የጋራ ኮሚቴ እንዲመሩ ይደረጋል፡፡

ለ. በጋራ ለሚሰሩ ስራዎች ከአባል ድርጅቶች የሚመደቡ አባላትን ምደባ የማፅደቅ የኢህአዴግ ስልጣን ሲሆን ከኢህአዴግ እወቀትና ስምምነት ውጭ ለጋራ ስራ የተመደበን አባል ለሌላ ስራ ማንሳት አይቻልም፡፡

ሐ. በዚህ ህብረ-ብሄራዊ አወቃቀር ውስጥ ተሳታፊ የሚሆኑት አባል ድርጅቶች የራሳቸውን አባላት ራሱን በቻለና ከኢህአዴግ መዋቅር ጋር ተመጋጋቢ በሆነ መልኩ ማደራጀት ይችላሉ፡፡

መ የጋራ ኮማቴዎቹ ተግባራቸውን የሚመሩበት ዝርዝር የአሰራር መመሪያ በኢህአደግ ጽ/ቤት ይወጣል፡፡

6. በየክልሉ የሚገኙ የሌሎች ብሄር ብሄረሰብ ድርጅት መዋቅሮችን በተመለከተ

ሀ. ብሄራዊ ድርጅቶች ባሉበት ክልል የሚገኙ የሌላ ብሄር አብዮታዊ ዴሞክራቶች በራሳቸው ብሄራዊ ድርጅት መዋቅር ተደራጅተው መንቀሳቀስ ይችላሉ፡፡

ለ. የእህት ድርጅቶች አባላት የሚደራጁባቸው መዋቅሮች ተልእኮ በአባላት እንዲሁም በብሄር ወይም ብሄረሰባቸው ውስጥ የሚገኙ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ማህበራዊ መሰረቶች ዘንድ የሕዝብ ግንኙነትና የድርጅት ተግባራት ማከናወን ነው:: እነዚህ አካላት የተለየ አስተዳደራዊ ሃላፊነት አይኖራቸውም::

ሐ. በየአካባቢው የሚገኙ የእህት ድርጅት መዋቅሮች ዋናውን የስምሪት አመራር የሚያገኙት የሚኖሩበትን ክልል ከሚመራው ብሄራዊ ድርጅት ይሆናል:: ክልሉን ለሚመራው ድርጅትም የስራ ዘገባቸውን በየወቅቱ ያቀርባሉ:: ከዚህ በተጓዳኝ ደግሞ ለራሳቸው ብሄራዊ ድርጅት ተመሳሳይ ሪፖርት ይልካሉ::

መ የዚህ ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ በኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይወጣል::

# ምዕራፍ ሁለት

# አባልነት

## አንቀጽ 8 የግንባሩ አባል ስለ መሆን

የሚከተሉትን መመዘኛዎች የሚያሟላ ድርጅት የኢህአዴግ አባል መሆን ይችላል።

1. የኢህአዴግን ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ ተቀብሎ በፅናት ተግባራዊ ለማድረግ ዝግጁ የሆነ፣ የተሟላ ውስጣዊ ዴሞክራሲያዊ አሰራር የሰፈነበት፣ ፕሮግራሙን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ማህበራዊ መሰረት ያለውና ተጨባጭ እንቅስቃሴ የሚያደርግ፣
2. ብሄራዊ የፖለቲካ ድርጅት ወይም በአንድ ክልል የሚገኙ በርካታ ብሄራዊ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ድርጅቶች የመሰረቱት ግንባር ወይም ህብረ ብሄራዊ ድርጅት የሆነ፣
3. በግንባሩ ህጎችና መመሪያዎች መሰረት እንደአስፈላጊነቱም በመዋቅሮቹ በመሳተፍ ተጨባጭ አስተዋጽኦ ለማድረግ ዝግጁ የሆነ፣
4. ለኢህአዴግ ተግባሮች ማስፈፀሚያ የሚሆን የገንዘብ መዋጮ ለመክፈል ዝግጁ የሆነ፣
5. የሙከራ ጊዜ አባልነቱን የጨረሰ ድርጅት

## አንቀጽ 9 የሙከራ ጊዜ አባልነት፣

1. ማንኛውም ድርጅት የግንባሩ አባል ከመሆኑ በፊት ለአንድ አመት በሙከራ ጊዜ ይቆያል።
2. አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ም/ቤቱ የሙከራ ጊዜውን ለተጨማሪ አንድ አመት ማራዘም ይችላል።

## አንቀፅ 10 አባልነትን ስለማፅደቅ

1. በሙከራ አባልነት የመቀበል ውሳኔ በኢህአዴግ ምክርቤት ይፀድቃል።
2. ሙሉ አባልነት የሚፀድቀው በኢህአዴግ ጉባኤ ይሆናል።

## አንቀጽ 11. የአባል ድርጅት መብት፣

ማንኛውም የግንባሩ አባል የሆነ ድርጅት የሚከተሉት መብቶች አሉት፣

1. በግንባሩ መተዳሪያ ደንብና አሰራር መሰረት በግንባሩ ውስጥ በውክልና በሚሞሉ የሀላፊነት ቦታዎች ሁሉ በእኩልነት የመወከል፣
2. በግንባሩ ደንብ መሰረት በምርጫ በሚወሰኑ የሀላፊነት ቦታዎች እጩዎችን የማቅረብ፣ ወይም ከመካከሉ መርጦ የመመደብና አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ደግሞ የመቀየር፣
3. የግንባሩ ደንብ በሚፈቅደው አሰራር መሰረት ማንኛውንም ሀሳብ በግንባሩ ውስጥ የማራመድና የማሰማት፣
4. በየትኛውም ቦታ በራሱ ድርጅታዊ መንገድ በህዝቡ ውስጥ የመስራት ማለትም የመመልመል፣ የማደራጀትና የማስተማር፣
5. በራሱ ውስጣዊ ድርጅታዊ አሰራር መሠረት የመስራት፣
6. በግንባሩ ንብረቶች በጋራ የመጠቀም፣
7. ግንባሩን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ በጋራ የመወሰን
8. አባልነቱን እስካልፈለገ ድረስ በዚህ መተዳደሪያ ደንብ በተገለፀው መሰረት በማንኛውም ጊዜ ግንባሩን የመልቀቅ

## አንቀጽ 12 የአባል ድርጅት ግዴታ፣

ማንኛውም የግንባሩ አባል የሆነ ድርጅት የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፣

1. የግንባሩን ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብ፣ መመሪያዎች፣ ውሳኔዎች እና እቅዶች ተግባራዊ ማድረግ እና ማክበር፣
2. የግንባሩን የአሰራርና የአመራር መርሆች ማክበርና መከተል፣
3. የግንባሩንና የአባል ድርጅቶችን ደህንነትና ምስጢር የመጠበቅ፣
4. በግንባሩ ውስጥ እንደድርጅት ተወክሎ በሚሳተፍባቸው አካላት መደበኛም ሆነ አስቸኳይ ስብሰባዎች የመሳተፍ፣ ምልዐተ-ጉባኤ ያለማጓደል፣
5. ፀረ-አንድነት አመለካከቶችና ተግባሮችን በጥብቅ መታገልና የግንባሩን አንድነት ማጠናከር፣

6. በአባል ድርጅቶች መካከል የሚኖረውን ግንኙነት በእኩልት የማጎልበትና የማጠናከር፣

## አንቀጽ 13 ከአባልነት ስለመሰረዝና አባልነትን በራስ ፈቃድ ስለመተው፣

1. በጥፋት ከአባልነት ማገድና መሰረዝ፣
   ሀ. ከላይ በአንቀጽ 12 የተዘረዘሩትን ግዴታዎች በተሟላ ሁኔታ የማይፈጽም ድርጅት ከግንባሩ አባልነት በጊዜያዊነት ሊታገድ ወይም ሙሉ በሙሉ ሊወገድ ይችላል።
   ለ. በጥፋተኛው ድርጅት ላይ ከአባልነት የማገድ ወይም የመሰረዝ ውሳኔ የሚተላለፈው በቅድሚያ ሂስ ተደርጎለት ግዴታውንም እንዲያሟላ እድል ተሰጥቶት ጥፋቱን ሳያስተካክል ከቀረ ብቻ ነው።
   ሐ. አንድን አባል ድርጅት ከአባልነት የማገድ ወይም የመሰረዝ ውሳኔ የሚተላለፈው በኢህአዴግ ምክር ቤት ይሆናል።
   መ. ከአባልነት የማገድ ወይም የመሰረዝ ርምጃ የተወሰደበት ድርጅት ለኢህአዴግ ቁጥጥር ኮሚሽን አቤቱታ የማቅረብና ጉዳዩ በጉባኤ እንዲታይለት የመጠየቅ መብት አለው። ሆኖም ጉባኤው ጉዳዩን የሚመለከተው ከሆነ የታገደው ወይም የተሰረዘው ድርጅት ተወካዮች አቤቱታቸውን ለማቅረብ ብቻ በጉባኤው ላይ እንዲገኙ ይደረጋል። በጉዳዩ ላይ ጉባኤው የሚያስተላልፈው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል።
   ሠ. ከአባልነት የተሰረዘ አባል ድርጅት በሂደት ስህተቱን አርሞ ወደ አባልነቱ ለመመለስ ሲጠይቅ ሁኔታው በጉባኤ ታይቶ ተቀባይነት ካገኘ እንደገና አባል ሊሆን ይችላል።

2. አባልነትን በራስ ፈቃድ ስለመተው፣
   ሀ. ማንኛውም የግንባሩ አባል የሆነ ድርጅት ለግንባሩ ምክር ቤት አሳውቆ በፈለገው ጊዜ ድርጅቱን መልቀቅ ይችላል።
   ለ. ከላይ «ሀ» የተጠቀሰው ቢኖርም የመልቀቁ ውሳኔ የሚፀናው እለቃለሁ ባለው ድርጅት ጉባኤ ሲወሰን ነው።

ሐ. ከላይ በ«ሀ» እና «ለ» የተጠቀሱት እንደተጠበቁ ሆነው ሌሎች አባል ድርጅቶችም በጉዳዩ ላይ አስተያየት ለመስጠት የሚችሉበት እድል የማመቻቸት ግዴታ አለበት::

3. ከአባልነት ማገድ፣ መሰረዝንና አባልነትን ስለመተው በተመለከተ የግንባሩ ምክር ቤት ዝርዝር መመሪያ ያወጣል::

## አንቀጽ 14 የሙከራ ጊዜ አባል ድርጅት መብት

1. ማንኛውም የግንባሩ የሙከራ ጊዜ አባል የሆነ ድርጅት የሚከተሉት መብቶች አሉት፣
    - ሀ. የግንባሩ ደንብ በሚፈቅደው አሰራር መሰረት በተለያዩ የውይይትና የስልጠና መድረኮች የመሳተፍ፣ ማንኛውንም ሀሳብ በግንባሩ ውስጥ የማራመድና የማሰማት፣
    - ለ. በግንባሩ ጉባኤና በምክርቤት ድምፅ አልባ ሆኖ የመሳተፍ፤
    - ሐ. በየትኛውም ቦታ በራሱ ድርጅታዊ መንገድ በህዝብ ውስጥ መስራት ማለትም የመመልመል፣ የመደራጀትና የማስተማር፣
    - መ. በራሱ ውስጣዊ ድርጅታዊ አሰራር መሰረት የመስራት፣
    - ሠ. የሙከራ ጊዜ አባልነቱን እስካልፈለገ ድረስ በማንኛውም ጊዜ ግንባሩን የመልቀቅ
2. ከላይ በንኡስ አንቀጽ 1 (መ) የተጠቀሰው ቢኖርም አባልነቱን መልቀቁን ለምክር ቤቱ ማሳወቅ ይጠበቅበታል::
3. የዚህ አንቀጽ አፈፃፀም ከላይ በአንቀጽ 13 (2) እና 13 (3) መሠረት ይመራል::

## አንቀጽ 15 የሙከራ ጊዜ አባል ግዴታዎች

ለኢህአዴግ ተግባራት ማስፈፀሚያ የሚሆን የገንዘብ መዋጮ ማድረግን ጨምሮ በዚህ የመተዳደሪያ ደንብ የአባል ድርጅት ግዴታዎች ተብለው የተዘረዘሩት በሙሉ የሙከራ ጊዜ አባልም ግዴታዎች ናቸው::

## አንቀፅ 16 ስለ አጋር ድርጅቶች

1. የሚከተሉትን የሚያሟላ ማንኛውም ብሔራዊ ድርጅት ከኢህአዴግ ጋር በአጋርነት መስራት ይችላል፤

   ሀ. ለሰላም፣ ለልማትና ለዴሞክራሲ በሚደረገው እንቅስቃሴ ከኢህአዴግ ጋር ተባብሮ ለመስራት ዝግጁ የሆነ፤

   ለ. በአካባቢው ምልአተ ህዝቡን በማንቀሳቀስ ከድህነትና ኋላቀርነት ለመላቀቅ በሚደረገው ትግል የመሪነት ሚና የሚጫወት፤

   ሐ. ጥገኛ አስተሳሰብና ድርጊቶችን በመታገልና ውስጠ ድርጅት አሰራሩን ዴሞክራሲያዊ በማድረግ በኩል ጥረት በማድረግ ላይ የሚገኝ፤

   መ. ለአብዮታዊ ዴሞክራሲ በጎ አመለካከት ያለው፤

2. ኢህአዴግ ከአጋር ድርጅቶች ጋር የጋራ በሆኑ ጉዳዮች ዙሪያ በጋራ ይሰራል፤ የጋራ አመራር ይሰጣል፤ አስፈላጊ የሆኑ የመደጋገፍ ተግባራትን ያከናውናል::
3. ከአጋር ድርጅቶች ጋር የሚኖረው ግንኙነት ዝርዝር አፈፃፀም ምክርቤቱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል::

# ምዕራፍ ሶስት

# ድርጅታዊ መዋቅር

## አንቀጽ 17 የግንባሩ የአመራር አካላትና ልዩ ልዩ መዋቅሮች፣

1. የኢህአዴግ ጉባኤ፣
2. የኢህአዴግ ምክር ቤት፣
3. የኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፣
4. የኢህአዴግ ሊቀመንበር፣
5. የኢህአዴግ ምክትል ሊቀመንበር፣
6. የኢህአዴግ የቁጥጥር ኮሚሽን፣
7. የኢህአዴግ ፅህፈት ቤት፣
8. የኢህአዴግ የፓርላማ መዋቅር
9. የኢህአዴግ የሴቶች ሊግ
10. የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ
11. የኢህአዴግ የበታች አካላት ናቸው፡፡

## አንቀጽ 18 የኢህአዴግ ጉባኤ፣

### 1. የጉባኤው አጠራርና አመሰራረት፣

ሀ. የኢህአዴግ ጉበኤ ከሁለት እስከ ሁለት ዓመት ተኩል ባለው ጊዜ ውስጥ ይካሄዳል፡፡ ሆኖም ምክር ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ጉባኤውን ከስድስት ወራት ላልለጠ ጊዜ ሊያረዝመው ይችላል፡፡

ለ. ጉባኤው ከአባል ድርጅቶች በእኩል ድምጽ በተወከሉ ጉባኤተኞች ይዋቀራል፣ የኢህአዴግ ምክር ቤት አባላትና የቁጥጥር ኮሚሽን አባላት በቀጥታ በጉባኤው ይሳተፋሉ፡፡

ሐ. የጉባኤው አባላት ከተወከሉበት ጉባኤ እስከሚቀጥለው ጉባኤ ድረስ ባለው ጊዜ በቋሚ ጉባኤተኛነት ይቆያሉ፡፡

መ. ለጉባኤው የሚያስፈልጉ ዝግጅቶች በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በሚቋቋም የጉባኤ አዘጋጅ ኮሚቴ አማካይነት ይካሄዳሉ።

ሠ. ጉባኤ አዘጋጅ ኮሚቴው ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴውና ከኢህአዴግ ምክር ቤት እንዲሁም ከአባል ድርጅቶች አጀንዳዎችን ይሰበስባል።

ረ. የጉባኤ ተሳታፊዎችን ቁጥርና ስብጥር አስመልክቶ መነሻ ሃሳብ በማዘጋጀት ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያቀርባል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል።

ሰ. ለኢህአዴግ ጉባኤ የሚወከሉ በየድርጅቱ ጉባኤ ይመረጣሉ። ሆኖም ቀደም ብሎ ጉባኤ ሊያካሂድ ያልቻለ ድርጅት ከታች ጀምሮ በሚካሄድ ምርጫ ጉባኤተኛ ሊያስወክል ይችላል።

## 2. አስቸኳይ ጉባኤ

ሀ. የግንባሩ ምክር ቤት በድምጽ ብልጫ ሲወስን ወይም ከአባል ብሄራዊ ድርጅቶች ግማሽ ያህሉ ሲጠይቁ ወይም ደግሞ የቋሚ ጉባኤ አባላት ጥያቄ አቅርበው ከቋሚ ጉባኤተኛው 50%+1 የድምፅ ድጋፍ ሲያገኙ አስቸኳይ ጉባኤ ይጠራል፣

ለ. የግንባሩ ቁጥጥር ኮሚሽን የቋሚ ጉባኤ አባላትን 1/3ኛ የድጋፍ ድምፅ ካገኘ አስቸኳይ ጉባኤ እንዲጠራ ለማድረግ ይችላል።

ሐ. አስቸኳይ ጉባኤ በሚጠራበት ጊዜ አስቀድሞ በተካሄደው መደበኛ ጉባኤ የተካፈሉት ጉባኤተኞች በቀጥታ እንዲሳተፉ ይደረጋል፣ የሚጓደል የሰው ሀይል ቢኖርም ምልዐተ-ጉባኤን የሚያዛባ እስካልሆነ ድረስ አዲስ ምርጫ አይካሄድም፣

መ. የአስቸኳይ ጉባኤ ምልአተ ጉባኤ 50%+1 ነው።

## 3. የጉባኤ ተግባርና ሀላፊነት፣

ሀ. ጉባኤው የግንባሩ የመጨረሻው ከፍተኛ የአመራር አካል ነው።

ለ. የግንባሩን ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ ያፀድቃል፣ ያሻሽላል። እንደአስፈላጊነቱም ይቀይራል።

ሐ. ግንባሩ የሚመራባቸውን አገር አቀፍ ፖሊሲዎችና ስትራቴጅ ይነድፋል።

መ. እስከ ቀጣዩ ጉባኤ ድረስ ግንባሩ የሚያከናውናቸውን አጠቃላይ ተግባራትና ግቦችን ይወስናል።

ሠ. የግንባሩን ምክር ቤትና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትን ቁጥር ይወስናል፡፡

ረ. የግንባሩን ምክር ቤትና የቁጥጥር ኮሚሽን ሪፖርቶችን ያዳምጣል፣ ይገመግማል፣ ውሳኔም ይሰጣል፡፡

ሰ. ከምክር ቤቱ በሚቀርብለት ሪፖርት መሰረት ሙሉ አባልነትን ያፀድቃል፡፡ ከአባልነት የመሰረዝ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

## 4. የጉባኤው አሰራር

ሀ. ጉባኤው መደበኛ ስራውን ከመጀመሩ በፊት በጉባኤ አዘጋጅ ኮሚቴው አማካይነት የጉባኤ ዝግጅቱን በተመለከተ ሪፖርት ቀርቦ እንዲፀድቅ ይደረጋል፣

ለ. ጉባኤው በፕሬዚዲየም ይመራል፡፡ የፕሬዚዲየሙ አባላት የየድርጅቱ ፀሃፊዎች ይሆናሉ፡፡

ሐ. በጉባኤው ላይ ለውይይት የሚቀርቡት አጀንዳዎች አስቀድመው በጉባኤተኛው እንዲፀድቁ ይደረጋል፤

# አንቀጽ 19 የኢህአዴግ ምክር ቤት አመሰራረት፣ ተግባርና ሀላፊነት እና አሰራር፣

## 1. የምክር ቤት አመሰራረት

ሀ. ምክር ቤቱ ከጉባኤው ቀጥሎ ያለው የግንባሩ ከፍተኛ አመራር አካል ነው፣

ለ. ምክር ቤቱ ከአባል ድርጅቶች በእኩል ቁጥር ይወከላል፤ የምክር ቤት አባላት ከየድርጅቱ ማእከላዊ ኮሚቴ አባላት ይመረጣሉ፣

ሐ. የእያንዳንዱ አባል ድርጅት ማዕከላዊ ኮሚቴ የምክር ቤት አባላትን የማውረድና በምትካቸውም ሌላ መርጦ የመተካት መብት ይኖረዋል፡፡

መ. የምክር ቤቱ ተጠሪነት ለኢህአዴግ ጉባኤ ነው፡፡

## 2. የምክርቤቱ ተግባርና ሃላፊነት

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ተግባርና ሃላፊነት ይኖሩታል::

ሀ. ከአንድ ጉባኤ እስከሚቀጥለው ጉባኤ ድረስ ግንባሩን በበላይነት ይመራል::

ለ. የጉባኤውን ውሳኔዎች መሰረት በማድረግ አገር አቀፍ ሚናና ትርጉም ባላቸው ጉዳዮች ላይ ፖሊሲዎችን ያወጣል፣ የድርጅቱን እቅዶች ይነድፋል፣

ሐ. በግንባሩ መተዳደሪያ ደንብ ትርጉም በሚሹ አከራካሪ ነጥቦች ላይ ውሳኔ ይሰጣል::

መ. መተዳደሪያ ደንቡን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ያወጣል፣ ያፀድቃል::

ሰ. ለግንባሩ የስራ ቅልጥፍና አስፈላጊ የሆኑ መዋቅሮችን ያደራጃል፣ ያሻሽላል::

ረ. የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴን ሪፖርት ያዳምጣል፣ ይገመግማል፣ ውሳኔ በሚሹ ነጥቦችም ላይ ይወስናል::

ሰ. በምክር ቤቱ አባላት 2/3ኛ ድምፅ እጩ አባልነትን ያፀድቃል፣ በተግባር ለሙከራ ጊዜ አባልነት ብቁ ሆኖ ያልተገኘን ድርጅት እጩ አባልነትን ይሰርዛል::

ሸ. የአባልነት ግዴታውን ያላሟላን ድርጅት እስከ ጉባኤ ድረስ ከአባልነት ያግዳል:: ከአባልነት የሚሰረዘው በጉባኤው ውሳኔ ይሆናል::

ቀ. ምክር ቤቱ ጥፋት በፈፀመ የምክር ቤቱ አባል ላይ በ2/3ኛ ድምፅ በጊዜያዊነት ከምክር ቤት አባልነት የማገድ እርምጃ ይወስዳል:: ውሳኔው በብሄራዊ ድርጅቱ ከፀደቀ በኋላ ይፀናል::

በ. የግንባሩን ሊቀመንበርና ምክትል ሊቀመንበር ይመርጣል::

ተ. የግንባሩን አመታዊ በጀት ያፀድቃል::

3. ስለ ምክር ቤቱ ስብሰባና አሰራር

ሀ. የምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በየ6 ወሩ ይካሄዳል።

ለ. ከላይ በ«ሀ» የተጠቀሰው ቢኖርም በ1/3ኛ የምክር ቤቱ አባላት ወይም በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ጥያቄ ሲቀርብ ምክር ቤቱ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያካሂድ ይችላል።

ሐ. በምክር ቤቱ በጋራ የተላለፈ ማንኛውም ውሳኔ በሁሉም ድርጅቶች ተፈፃሚ ይሆናል።

መ. የምክር ቤቱ ስብሰባ በግንባሩ ሊቀመንበር ይመራል፣

ሠ. ተናጠል ድርጅትን የሚመለከት ጉዳይ እንደአስፈላጊነቱ በሚመለከተው ድርጅት ማዕከላዊ ኮሚቴ ብቻ ሊወሰን ይችላል፣

## አንቀጽ 20 የኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አመሰራረት፣ ተግባርና ሀላፊነት እና አሰራር፣

1. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አመሰራረት፣

ሀ. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በሁሉም አባል ድርጅቶች የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት በእኩል ድምጽ ይቋቋማል።

ለ. የእያንዳንዱ ድርጅት ማዕከላዊ ኮሚቴ አግባብ መስሎ በታየው ጊዜ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተወካዮቹን ሊቀይር ይችላል፣

ሐ. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለኢህአዴግ ምክር ቤት ነው።

መ. ከየድርጅቱ የተወከሉ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ተጠሪነት ለኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ለየድርጅቶቻቸው ማዕከላዊ ኮሚቴዎች ነው፣

2. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተግባርና ሀላፊነት

ሀ. የምክር ቤቱን ውሳኔዎችና መመሪያዎች ያስፈፅማል።

ለ. የልዩ ልዩ የጋራ አካላትን ስራዎችና እንቅስቃሴዎች ይመራል።

ሐ. ከብሄራዊ ድርጅቶች ጋር በመመካከር ለጋራ ተቋማት የሚያስፈልግ የሰው ሃይል ምደባ ያካሂዳል።

መ. ለምክር ቤቱ ስብሰባዎች ሪፖርትና አጀንዳ ያዘጋጃል።

ሠ. እንደአስፈላጊነቱ ጊዜያዊ አካላትን አዋቅሮ ያሰራል።

ረ. የምክር ቤት ውሳኔዎችን ለማስፈፀም የሚረዱ የስራ መመሪያዎችን ያወጣል።

ሰ. በግንባሩ ስም ውል ይዋዋላል።

ሸ. ሁሉም አባል ድርጅቶች በእኩልነት የሚወከሉበት የጉባኤ አዘጋጅ ኮሚቴ ያቋቁማል፣ ዝርዝር የስራ መመሪያም አዘጋጅቶ ይሰጣል።

## 3. ስለ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ስብሰባና አሰራር

ሀ. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው መደበኛ ስብሰባ በየ3 ወሩ ይካሄዳል።

ለ. ሊቀመንበሩ ወይም ምክትል ሊቀመንበሩ፣ እንዲሁም ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው አባላት 1/3ኛው አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ሲጠይቁ አስቸኳይ ስብሰባ ሊካሄድ ይችላል፣

ሐ. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ስብሰባ አስቸኳይ ጉዳዮች ከሌሉ በቀር አስቀድሞ በተዘጋጁ ጽሑፎች ላይ የተመሰረተ ይሆናል።

መ. በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የተላለፈ ማንኛውም ውሳኔ በሁሉም የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ተፈፃሚ ይሆናል፣

ሰ. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ስብሰባ በግንባሩ ሊቀመንበር ይመራል።

## አንቀጽ 21 የኢህአዴግ ሊቀመንበር ተግባርና ሃላፊነት

1. የግንባሩን የምክር ቤትና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባዎችን በሊቀመንበርነት ይመራል።
2. የምክር ቤቱን ውሳኔዎች ያስፈጽማል። የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴውን እንቅስቃሴ ያስተባብራል።
3. ግንባሩን በመወከል ከተለያዩ አካላት ጋር ግንኙነት ያደርጋል።
4. የስራ ሪፖርቱን ለስራ አስፈፃሚው ኮሚቴ ያቀርባል፣ ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባዎች አጀንዳ ያዘጋጃል።
5. የማእከላዊ አካላትን ስራዎች ያስተባብራል።
6. በምክር ቤቱና በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የሚሠጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## አንቀጽ 22 የኢህአዴግ ምክትል ሊቀመንበር ተግባርና ሀላፊነት

1. የግንባሩ ሊቀመንበር በማይኖርበት ጊዜ ሊቀመንበሩን ተክቶ ይሰራል፡፡
2. በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴውና በሊቀመንበሩ የሚሰጡትን ስራዎች ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ 23 የኢህአዴግ የቁጥጥር ኮሚሽን አመሰራረት፣ ተግባር፣ ሀላፊነትና አሰራር፣

### 1. የኮሚሽኑ አመሰራረት፣

ሀ. የኢህአዴግ ቁጥጥር ኮሚሽን በእያንዳንዱ አባል ድርጅት ጉባኤ በሚወከሉ ሁለት ሁለት አባላት ይቋቋማል፡፡

ለ. የኮሚሽኑ ተጠሪነት ለኢህአዴግ ጉባኤ ነው፡፡

### 2. የኮሚሽኑ ተግባርና ሀላፊነት

ሀ. ኮሚሽኑ የአባል ድርጅቶችና በጋራ ተቋማት ውስጥ ተመድበው የሚሰሩ አባላት መብቶች መከበራቸውን ይከታተላል፡፡ በጋራ ኮሚቴዎች አማካኝነት የሚፈፀም የመብት መጣስን በተመለከተ የሚቀርቡለትን ቅሬታዎች ተቀብሎ ያጣራል፡፡ የራሱን የውሳኔ ሃሳብም ያሳልፋል፡፡

ለ. የግንባሩ ንብረትና ገንዘብ በትክክል መያዙንና በተቀመጠለት የአሰራር ስርዓት መሰረት ጥቅም ላይ መዋሉን ይከታተላል፡፡ በዚህ ረገድ የሚታዩ ጉድለቶችን ለማስተካከል የሚያስችል የመፍትሄ ሃሳብ ያቀርባል፡፡

ሐ. ኮሚሽኑ በ2/3ኛ ድምፅ አስቸኳይ ጉባኤ መጠራት አለበት ብሎ ካመነና ከኢህአዴግ ቋሚ ጉባኤ አባላት 1/3ኛ የድጋፍ ድምፅ ካገኘ አስቸኳይ ጉባኤ እንዲጠራ ያደርጋል፡፡

መ. ኮሚሽኑ ባሳለፈው ውሳኔ ላይ ከኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ጋር የሀሳብ አንድነት ከተያዘበት ውሳኔው ተግባራዊ ይሆናል፡፡ ልዩነት ከተከሰተ ልዩነቱ ወደ ኢህአዴግ ምክር ቤት ይተላለፋል፡፡ ምክር ቤቱ የሚያሳልፈው ውሳኔ እስከ ጉባኤ ድረስ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

ሠ. ግንባሩን ወይም አባል ድርጅቶቹን የሚመለከቱ መጣራት የሚገባቸው ጉዳዮች ሲኖሩ በግንባሩ ምክር ቤት ጥያቄ እንደነፃ አጣሪ አካል ሆኖ ያገለግላል፣ ሪፖርቱንም ለምክር ቤቱ ያቀርባል።

ረ. እርምጃ ሊወሰድባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ሲኖሩ ከሚመለከታቸው የግንባሩ አካላት ጋር ግንኙነት በማድረግ ያስፈጽማል። ከግንባሩ ምክር ቤትና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ጋር የቅርብ ግንኙነት ይመሰርታል።

ሰ. ኢህአዴግ በቀጥታ ከሚከታተላቸው ክፍሎች በየደረጃው የራሱን የበታች መዋቅሮች ያደራጃል፣ እነዚህ አካላት የሚመሩባቸውን መመሪያዎች ጨምሮ ለስራው የሚጠቅሙ ሌሎች መመሪያዎችን ማውጣት ይችላል።

ሸ. ጥፋት በሚፈፅሙ አባሎቹ ላይ የዲስፕሊን እርምጃ መውሰድ ይችላል። አባሉን ማገድ ወይም ከስልጣኑ ማውረድ የሚችለው በአባላቱ 2/3ኛ ድምጽ ይሆናል።

ቀ. ስለስራው ለግንባሩ ጉባኤ ሪፖርት ያቀርባል።

በ. ኮሚሽኑ ከብሄራዊ ድርጅቶች የቁጥጥር ኮሚሽኖች ጋር በቅንጅት ይሰራል።

ተ. ኮሚሽኑ ከመካከሉ ሊቀመንበር፣ ምክትል ሊቀመንበርና ፀሀፊ መርጦ ለጉባኤው ያስታውቃል፣

ቸ. ኮሚሽኑ ይህን የመተዳሪያ ደንብ መሰረት በማድረግ የራሱን አሰራርና መመሪያዎች ያወጣል።

## 3. ስለኮሚሽኑ ስብሰባ እና አሰራር፣

ሀ. የኮሚሽኑ መደበኛ ስብሰባ በየስስት ወሩ ይካሄዳል።

ለ. የኮሚሽኑ ሊቀመንበርና ፀሀፊ እንዲሁም ቋሚ ፅህፈት ቤት ይኖራቸዋል። ከኮሚሽን ሀላፊነታቸው ጋር የሚጋጩ የግንባሩን ተግባራት በተደራቢነት አይሰሩም፣

ሐ. የፅህፈት ቤቱ አባላት ተግባርና ሀላፊነታቸውን በተመለከተ ዝርዝር ሪፖርት ለኮሚሽኑ ያቀርባሉ፣

መ. ኮሚሽኑ የራሱን ዓመታዊ እቅዶች እያዘጋጀ ተግባራቱን ይመራል፣

## አንቀጽ 24 የኢህአዴግ ጽህፈት ቤት

### 1. የጽህፈት ቤቱ አመሰራረት

ሀ. የኢህአዴግ ጽህፈት ቤት መደበኛና ደጋፊ የህዝብ ግንኙነትና የድርጅት ስራዎችን አዋህዶ ለማስፈፀም በሚያስችል መልክ ይደራጃል፡፡

ለ. በኢህአዴግ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በሚመደቡ ሃላፊና ምክትል ሃላፊ ይመራል፡፡

ሐ. ከላይ በ«ለ» የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ በጽህፈት ቤቱ ሃላፊ፣ በምክትል ሃላፊና በተለያዩ የስራ ሃላፊዎች የተዋቀረ አመራር ኮሚቴ ይደራጃል፡፡

መ. የጽህፈት ቤቱ ተጠሪነት ለኢህአዴግ ሊቀመንበር ይሆናል፡፡

### 2. የጽህፈት ቤቱ ተግባርና ሃላፊነት

ሀ. ጽህፈት ቤቱ በግንባሩ ውስጥ የሚካሄደውን የህዝብ ግንኙነት፣ የድርጅት፣ የፋይናንስና አስተዳደር ስራ በሃላፊነት ያከናውናል፡፡ የግንባሩ የህዝብ ግንኙነትና የድርጅት ሥራዎች ማዕከል ሆኖ ይንቀሳቀሳል፡፡

ለ. በአገር ውስጥና በውጭ አገር በመደበኛና ደጋፊ መንገዶች የሚካሄደውን የህዝብ ግንኙነትና የድርጅት ተግባራትን ያከናውናል፤ ይመራል፡፡

ሐ. የኢህአዴግ ምክር ቤትና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴን ውሳኔዎችን መሰረት በማድረግ የግንባሩን የህዝብ ግንኙነትና የድርጅት ስራ ያቅዳል፤ ያስፈፅማል፡፡ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡

መ. በብሄራዊ ድርጅቶች አማካይነት ለሚካሄደው የህዝብ ግንኙነትና የድርጅት ስራ ድጋፍና አጠቃላይ አመራር ይሰጣል፤ ስራውን ያስተባብራል፡፡

ሠ. በጋራ እንደ ኢህአዴግ የሚንቀሳቀሱ ስራዎችንና አካላትን በቀጥታ ይመራል፡፡

ረ. የግንባሩን የእቅድ አፈፃፀም ለህዝብ ያስተዋውቃል፤ ከህዝብ ለግንባሩ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ምክርቤቱን በመወከል ምላሽ ይሰጣል፡፡

ሰ. በኢህአዴግ ምክር ቤት የፀደቀውን በጀት ያስተዳድራል፤

ሸ. በኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ በሚፀድቅ መመሪያ መሠረት የግንባሩን ፋይናንስና ንብረት እንዲሁም የጽህፈት ቤቱን ሠራተኞች ያስተዳድራል።

ቀ. የግንባሩ ሰነዶች በአግባቡ መያዛቸውንና ጥቅም ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል።

በ. ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ከሊቀመንበሩ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ኢህአዴግን ወክሎ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር ግንኙነት ያደርጋል፤.

ተ. ግንባሩን በመወከል ይከሳል ይከሰሳል።

ቸ. ስለ ስራው አፈፃፀም ለኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ለሊቀመንበሩ ሪፖርት ያቀርባል።

## 3. የጽህፈት ቤቱ አሰራር

ሀ. የጽህፈት ቤቱ አመራር ኮሚቴ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል።

ለ. ጽህፈት ቤቱ የስራ አፈፃፀሙን በሚመለከት መደበኛና ወቅታዊ ሪፖርቶችን ለሊቀመንበሩ ያቀርባል።

ሐ. ጽህፈት ቤቱ ከአባል ድርጅቶች ጋር የሚኖረው ግንኙነት በአባል ድርጅቶች ጽህፈት ቤት በኩል ይሆናል።

መ. የጽህፈት ቤቱ ዝርዝር አሰራር፣ ተግባርና ሃላፊነት አስመልክቶ የኢህአዴግ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

ሠ. በጽህፈት ቤቱ የሚመደቡ ሃላፊዎችም ሆነ የድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ምደባ በተቻለ መጠን የሁሉም አባል ድርጅቶችን ተዋጽኦ ከግምት ያስገባ ይሆናል።

## 4. የኢህአዴግ ጽህፈት ቤት ሃላፊ

ሀ. የግንባሩ ጽህፈት ቤት ሃላፊ ተጠሪነት ለግንባሩ ሊቀመንበር ነው።

ለ. የኢህአዴግ ጽህፈት ቤትን የህዝብ ግንኙነትና የአደረጃጀት እንዲሁም የፋይናንስና የሰው ሃይል አስተዳደር ሥራዎችን ያስተባብራል ይመራል፤

ለ. ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ከሊቀመንበሩ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ከሦስተኛ ወገኖች ጋር የሚኖረውን ግንኙነት ይፈፅማል፤

ሐ. የጽህፈት ቤቱን በጀትና ንብረት በበላይነት ያስተዳድራል፣

መ. ስለ ጽህፈት ቤቱ የሥራ እንቅስቃሴ ለሊቀመንበሩ ወቅታዊ ሪፖርት ያቀርባል፤

ሸ. የኢህአዴግ ጽህፈት ቤትን በመወከል ውል ይዋዋላል፡፡

## 5. የጽህፈት ቤቱ ምክትል ሃላፊ

ሀ. የግንባሩ ጽህፈት ቤት ምክትል ሃላፊ ተጠሪነቱ ለጽህፈት ቤቱ ሃላፊ ነው፤

ለ. የጽህፈት ቤቱ ሃላፊ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፤

ሐ. አንድ የተለየ የስራ ዘርፍ እንዲመራ ይደረጋል፡፡

መ. ሌሎች ከግንባሩ ሊቀመንበርም ሆነ ከጽህፈት ቤቱ ሃላፊ የሚሰጡ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ 25 ለኢህአዴግ ጽህፈት ቤት ተጠሪ ስለሆኑ አደረጃጀቶች

1. ኢህአዴግ የሚመራባቸው አጠቃላይ የአደረጃጀት መርሆዎች እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉት አደረጃጀቶች ድርጅታዊ ተግባራቸውን በሚመለከት ለኢህአዴግ ጽህፈት ቤት ተጠሪ ይሆናሉ፡-

ሀ. ለፌዴራል መንግሥት ተጠሪ በሆኑ ከተሞችና መ/ቤቶች የሚገኙ የኢህአዴግ መዋቅሮች፤

ለ. በውጭ አገር በሚገኙ ኢትዮጵያውያን ዘንድ የሚካሄድ ስራ

ሐ. በዩኒቨርስቲዎችና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እንዲሁም በላብአደሮች የሚኖር የኢህአዴግ መዋቅር፤

2. ከላይ በአንቀጽ 25.1 የተጠቀሱት መዋቅሮች አሰራርና የክትትል አግባብ በኢህአዴግ ጽህፈት ቤት በሚወጣ ዝርዝር መመሪያ መሠረት ይወሰናል፡፡

## አንቀጽ 26 የኢህአዴግ የፓርላማ መዋቅር

1. የፓርላማ ኢህአዴግ መዋቅር አደረጃጀት

ሀ. በፌዴራል የህዝብ ተካዮች ምክርቤት ውስጥ ያሉ የኢህአዴግ አባላት በኢህአዴግ የፓርላማ መዋቅር ይደራጃሉ፡፡

ለ. መዋቅሩ በኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በሚመደብ የአመራር ኮሚቴ ይመራል።

ሐ. የፓርላማ ኢህአዴግ መዋቅር ተጠሪነት ለኢህአዴግ ሊቀመንበር ይሆናል።

መ. የፓርላማ መዋቅሩ ከኢህአደግ ጽ/ቤት ጋር የስራ ግንኙት ይኖረዋል።

2. የፓርላማ መዋቅር ተግባርና ሃላፊነት

ሀ. በፓርላማው ውስጥ ያሉ  የኢህአዴግ አባላት በአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብና ተግባር እንዲገነቡ ያደርጋል።

ለ. የኢህአዴግ አባላት በፓርላማው ውስጥ ለልማት፣ ለዴሞክራሲና ለሰላም በግንባር ቀደምነት የሚንቀሳቀሱበትን ሁኔታ ያረጋግጣል።

ሐ. የመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ስርዓቱ ተጠናክሮ እንዲቀጥል የኢህአዴግ አባላት ንቁ ተሳታፊ የሚሆኑበትን ሁኔታ ያረጋግጣል።

መ. ከኢህአዴግ ስራ አስፈሚ ኮሚቴ የሚሰጠውን አመራር መሰረት በማድረግ በፓርላማው ውስጥ የሚሰሩ የህዝብ ግንኙነትና የድርጅት ስራዎችን ያቅዳል፣ ያስፈፅማል።

ሠ. ስለ ስራው ለኢህአዴግ ሊቀመንበር ሪፖርት ያቀርባል።

3. የፓርላማ መዋቅሩን ዝርዝር አሰራርና ተግባርና ሃላፊነት በሚመለከት በኢህአደግ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተጨማሪ መመሪያ ይወጣል።

## አንቀፅ 27  የኢህአዴግ የሴቶች  ሊግ

**1. የኢህአዴግ ሴቶች ሊግ አደረጃጀት**

ሀ. የኢህአዴግ ሴቶች ሊግ የኢህአዴግ አባል በሆኑት ብሔራዊ ድርጅቶች የሴቶች ሊጐች ይመሰረታል።

ለ. የኢህአዴግ ሴቶች ሊግ ከኢህአዴግ ጋር በጥብቅ የተሳሰረና የኢህአዴግ አንድ አካል ሆኖ ይደራጃል፣

ሐ. ከኢህአዴግ አደረጃጀት ተመሳሳይ በሆነ መልኩ በየደረጃው ካለ የኢህአዴግ መዋቅር በተጓዳኝ ይዋቀራል።

መ. በብሄራዊ ድርጅቶች የሴቶች ሊግ አመራር በእኩል ቁጥር የሚወከል የኢህአዴግ የሴቶች ሊግ ምክርቤትና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይኖረዋል፡፡

ሠ. የኢህአዴግ የሴቶች ሊግ ዝርዝር አደረጃጀት፣ ተግባርና ሃላፊነት እንዲሁም አሰራር በራሱ በሊጉ ጉባኤ ይፀድቃል፡፡

2. **የኢህአዴግ ሴቶች ሊግ መብቶች**

ሀ. የኢህአዴግ መርህን በማይፃረር አኳኋን የራሱ መተዳደሪያ ደንብ፣ አመራር፣ ራሱን የቻለ መዋቅር ይኖረዋል፤

ለ. በኢህአዴግ ጉባኤ፣ ምክር ቤትና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሊጉ ውክልና እንዲኖረው ይደረጋል፤ ዝርዝሩ የኢህአዴግ ምክር ቤት በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

ሐ. እንደ ማህበር በኢህአዴግ አሰራሮችና ተግባራት ዙሪያ አስተያየት የመስጠት፣ ሂስ የማቅረብና መልስ የማግኘት መብት አለው፡፡

3. **የኢህአዴግ ሴቶች ሊግ ግዴታዎች**

ሀ. የኢህአዴግን የልማት፣ የዴሞክራሲና የሰላም ስትራተጅ በአገር አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ ለማድረግ የመንቀሳቀስ ግዴታ አለበት፤

ለ. የኢትዮጵያ ሴቶች ከሁሉም አይነት ጭቆና በትግላቸው ነፃ እንዲወጡ የትግል መሳሪያ ሆኖ ማገልገል ይኖርበታል፡፡

መ. የኢህአዴግን ውሳኔዎች ማክበርና ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

## አንቀጽ 28 የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ

1. **የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ አደረጃጀት**

ሀ. የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ በኢህአዴግ አባላት ብሔራዊ ድርጅቶች የወጣት ሊጐች ይመሰረታል፡፡

ለ. የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ የኢህአዴግ ጋር በጥብቅ የተሳሰረና የኢህአዴግ አንድ አካል ሆኖ ይደራጃል፤

ሐ. ከኢህአዴግ አደረጃጀት ተመሳሳይ በሆነ መልኩ በየደረጃው ካለ የኢህአዴግ መዋቅር በተጓዳኝ ይዋቀራል፡፡

መ. ከኢህአዴግ አባል ድርጅቶች የወጣቶች ሊግ አመራር በእኩል ቁጥር የሚወከል ምክርቤትና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይኖረዋል፡፡

ሰ. የሊጉ ዝርዝር አደረጃጀት፣ ተግባርና ሃላፊነት እንዲሁም አሰራር በራሱ ጉባኤ ላይ በሚፀድቅ መተዳደሪያ ደንብ ይወሰናል፡፡

4. **የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ መብቶች**

ሀ. የኢህአዴግ መርህን በማይፃረር አኳኋን የራሱ መተዳደሪያ ደንብና ነፃ እንቅስቃሴ ይኖረዋል፤

ለ. በኢህአዴግ ጉባኤ፣ ምክር ቤትና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባዎች ሊጉ ውክልና እንዲኖረው ይደረጋል፤ ዝርዝሩ የኢህአዴግ ምክርቤት በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

ሐ. በኢህአዴግ አሰራሮችና ተግባራት ዙሪያ እንደ ማህበር አስተያየት የመስጠት፣ ሂስ የማቅረብና መልስ የማግኘት መብት አለው፡፡

5. **የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ግዴታዎች**

ሀ. የኢህአዴግን የልማት፣ የዴሞክራሲና የሰላም ስትራተጅ በአገር አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ ለማድረግ የመንቀሳቀስ ግዴታ አለበት፤

ለ. የኢትዮጽያ ወጣቶች ብቁ አገር ተረካቢ እንዲሆኑ፣ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብና ተግባር እንደታነፁ በፅናት መንቀሳቀስ፤

ሐ. የኢህአዴግን ውሳኔዎች ማክበርና ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

## አንቀፅ 29. የኢህአዴግ የበታች አካላት፡-

### 1. የበታች አካላት አደረጃጀትና አሰራር፡-

ሀ. ከአንቀፅ 17 እስከ 24 ድረስ ከተዘረዘሩት የኢህአዴግ የአመራር አካላትና መዋቅሮች በተጨማሪ እንደየአስፈላጊነቱ ሌሎች የግንባሩ አካላት ሊዋቀሩ ይችላሉ፡፡

ለ. የግንባሩን አበይት ተግባራት የሚያከናውኑና በባህሪያቸው ቋሚ የሆኑ አካላት በምክር ቤቱ ውሳኔ ይዋቀራሉ፡፡ ሊፈርሱና ተግባራቸውም ሊሻሻል የሚችለው በግንባሩ ምክር ቤት ውሳኔ ይሆናል፡፡

ሐ. ለተወሰነ ጊዜያዊ ተግባር የሚያገለግሉ አካላት በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውሳኔ መዋቀር ይችላሉ፡፡ ተልእኮአቸውን እንደፈፀሙም የሚፈርሱ ይሆናሉ፡፡

መ. ኢህአዴግ በጋራ በሚከታተላቸው የጋራ አካላት ውስጥ የቁጥጥር ኮሚሽን የበታች አካላት በኮሚሽኑ ይመሰረታሉ፡፡ ሊፈርሱ፣ ተግባርና ሀላፊነታቸው ሊሻሻል የሚችለውም በኮሚሽኑ ብቻ ይሆናል፡፡

ሠ. የበታች አካላት ምስረታ የአባል ድርጅቶችን ተሳትፎ ባረጋገጠ አኳኋን እንዲፈፀም ይደረጋል፡

### 2. የበታች አካላት ተግባርና ሀላፊነት፡-

ሀ. የበታች አካላት ተጠሪነት ላዋቀሯቸው አካላት ይሆናል፡፡ ማእከላዊ አካላት ከሆኑ ተጠሪነታቸው ለግንባሩ ጽ/ቤት ወይም እንደሁኔታው ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይሆናል፡፡

ለ. የበታች አካላት የተሰጣቸውን ተግባርና ሀላፊነት በአግባቡ የመፈፀም ግዴታ አለባቸው፣ ስለስራቸውም ለበላይ አካል ዘገባ ያቀርባሉ፣ የበላይ አካልን መመሪያዎች ይፈፅማሉ፣ ድጋፍ በሚያስፈልጋቸው ጊዜ ጠ ይቀው ማግኘት ይችላሉ፡፡

ሐ. የበታች አካላት ኮሚቴያዊ የጋራ አሰራርና ግለሰባዊ ሀላፊነት ይኖራቸዋል፡፡ ዴሞክራሲያዊ አሰራርን ይከተላሉ፣ የሂስ፣ ግለሂስና የግምገማ አሰራርን ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡

መ. ከየድርጅቶቹ የተወከሉ አባላት ስለአካላቸው የስራ እንቅስቃሴ ለወከላቸው ድርጅት ዘገባ የማቅረብ መብት አላቸው:: ሆኖም ስለስራቸው መመሪያ የሚያገኙት ካዋቀራቸው አካል ብቻ ነው::

ሠ. ለበታች አካላት ዝርዝር የአሰራር መመሪያዎች በግንባሩ ጽ/ቤት ወይም እንደሁኔታው በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይወጣላቸዋል::

ረ. የቁጥጥርና ኦዲት ኮሚሽንም በስሩ ላሉ የበታች አካላት አስፈላጊውን መመሪያ ያዘጋጃል::

# ምዕራፍ አራት

# ማጠቃለያ ድንጋጌዎች

## አንቀፅ 30. የግንባሩ የፋይናንስ ምንጮች፦

የግንባሩ የፋይናንስ ምንጮች የአባል ድርጅቶች መዋጮ፣ በአገሪቱ የፓርቲ ህግ መሰረት የኢትዮጵያውያን ደጋፊዎች ርዳታና ሌሎች የገቢ ምንጮች ናቸው።

## አንቀፅ 31. መመሪያ የማውጣት ስልጣን፦

በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ለተለያዩ አካላት የተሰጠው ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የኢህአዴግ ምክር ቤት ይህን መተዳደሪያ በስራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ያወጣል።

## አንቀፅ 32. መተዳደሪያ ደንቡን ማሻሻል፣ መቀየርና መሻር፦

ይህን መተዳደሪያ ደንብ ሊያሻሽል፣ ሊቀይርና ሊሽር የሚችለው የኢህአዴግ ጉባኤ ብቻ ነው።

## አንቀፅ 33. አውጭው አካል፦

ይህ መተዳደሪያ ደንብ በኢህአዴግ 6ኛ ድርጅታዊ ጉባኤ ተሻሽሎ የወጣ ነው።

## አንቀፅ 34. የተሻረ ህግ፦

ይህ መተዳደሪያ ደንብ ከፀናበት ቀን ጀምሮ በኢህአዴግ 5ኛ ድርጅታዊ ጉባኤ ፀድቆ በስራ ላይ የነበረው መተዳደሪያ ደንብ ተሽሮ በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ተተክቷል።

## አንቀፅ 35. መተዳደሪያ ደንቡ የሚፀናበት ቀን፦

ይህ መተዳደሪያ ደንብ ከመስከረም 16 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።